# አሓዝ ቢደረደር ለሕዝብ ምኑ ነው?

የወያኔ ሟቹ መሪ የአክሱም ሓውልት ለወላይታ ሕዝብ ምኑ ነው ያለውን አልረሳንም። ግብዙ ዘረኛ ኢትዮጵያዊነት የለም ሲለን ነበር። አክሱምም ሼክ ሁሴንም ላሊበላም ቁልቢም፤ የባሌ ታሪካዊ ዋሾዎችም፤ ጭላዳም ቀይ ቀበሮም ሁሉ የመላ ኢትዮጵያ ቅርሶችና መለያዎች ናቸው ። ይመለከቱናል። የማይመለከተን ግን የወያኔ ማፈሪያ ዘረኝነት ነው። ግድ የሌለን ግን ወያኔ ኤኮኖሚው አደገ እያለ የሚደረድረው የሀሰት አሀዝ ነው።

ወያኔና ጭፍሮቹ - አጫፋሪዎቹ በሞላ የሀገራችን ኤኮኖሚ በየአመቱ ከ 9 በመቶ እስከ 11 በመቶ እያደገ ነው ብለው ይለፍፉብናል። አሀዙንም ይደረድራሉ -- ግን ይህ ሁሉ ምን ማለት ነው? ኤኮኖሚው ይደግ ይመንደግ ግን ለህዝብ ምን ትርጉም አለው? እድገቱስ ሀቅ ነው ወይስ ማስተኛና ሀሰት? የአንድ ሀገር ኤኮኖሚ አደገ እየተባለ፣ ከ 91 ሚሊዮን ሕዝብ ውስጥ

- አብዛኛው እየተራበ
- ከ 80 በመቶው በላይ ንጹህ የሚጠጣው ውሀ እያጣ፤
- 99 በመቶ የከተማ ነዋሪው ተገቢ መኖሪያ አጥቶና ብዙ መቶ ሺዎች መንገድ አዳሪ ሆነው፤
- ብዙ ሚሊዮኖች ንጹህ የሚጠጣ ውሀ፤ መብራትና ተገቢ መጸዳጃ ቦታ አጥተው፤
- 95 ከመቶው በላይ ተገቢ የጤና እንክብካቤ ማግኘት ተስኖት፤
- አርሶ አደሩ በድህነት ማቆ፤
- ተትረፈረፈ የተባለው ቆሳቁስ ሁሉ ከአብዛኛው የግዢ አቅዋም በላይ ሆኖና የኑሮ ውድነት ሰማይ ነክቶ፤
- ስራ አጥነት የሚሊዮኑ ዕጣ ፈንታ ሆኖ፤
- ቀቢጸ ተስፋ ሀገሪቷን አሽመድምዶ

ባለበት የ እድገት አሃዝ ትርጉም አልባና ዋጋ ቢስ መሆኑ ግልጽ ነው። ባለፉት ስርዓት ሕዝብ ሲባል ጥቂቶች ነበሩ። ለሰፊው ሕዝብ ቆምኩ ያለው አረመኔው የደርግ አገዛዝም ቢሆን ሕዝብ ሲል ራሱን መሆኑ ባካሄደው ፍጅትና ጭፍጨፋ ግልጽ አድርጓል። ወያኔ እንኳን ሲጀመርም ለእኔ ህዝብ ወርቅ የሆነው የራሴ ክልል ሕህዝብ ነው ቢልም ለነዚህም ቆሞ ብዙሀኑን ሲጠቅማቸው መቶ በመቶ አልታየም -- ሁሉም ገገር ከፍል የሚያስቀድመው ራሱን ብቻ ነው። በዚህ በዚያ ቀለበት መንገድ ተሰራ፤ ሽታታ ኮንዶሚኒየም ሕንጻ ቆመ፤ የከተማ ባቡር ሊገነባ ነው፤ ግድቡ ግንባታው ጦፈ ወዘተ ቢባልም በተጨባጭ ከሕዝብ ኑሮ መሻሻል አንጻር ለውጥና መሻሻል ሳይሆን መሽቆልቆልና ውድቀት ነው ሰፍኖና አፍኖን ያለው። እድገት የሚለካው በሕዝብ ደህንነትና ብልጽግና ነው። የጥቂቶች መንደላቀቅ የሚሊዮኖች አይደለምና ገዢ ተብየዎች በሙስና ሲጨማለቁና ሲምነሸነሹ ሕዝብ አለፈለት ማለት የሚቻል አይደለም። 95 በመቶ በላይ የኢትዮጵያ ህዝብ ሀገሪቷን ሙስና ጎድቷታል ብሎ ያምናል። ያን ያህል ሕዝብ ደግሞ ኑሮአችን ከበፊቱ ይበልጥ ተበላሽቷል እያለ ነው። በድሀ ሀገሮች ተርታ ኢትዮጵያ ከባለበባቸው አንድዋ ናት። የጤና ጥበቃ ሲነሳም ሚዛኗ ውድቅ ነው። በሁሉም መስከ ሚዛኗ ሲፈረጅ አሳፋሪ ሆኖ ሳለ ኤኮኖሚዋ በጣም አደገ ብሎ ልፈፋው አሰቃቂ ውሸት ሆኖ ይገኛል። የወያኔ አሃዝ ህዝብን ከረሃብና ስቃይ አያድነውም። ሊያድነውም አይችልም። ለዚህም ነው ወያኔና ደጋፊዎቹ ኢትዮጵያ ኣደገች ተመነደገች ብለው የሚያቅራሩት ከተራ ማወናበጃ

ውጪ ምንም ትርጉምና ሚዛን የማይኖረው። ሀቁ ይነገር ከተባለ ደግሞ ወያኔ ሲመቸው ሕዝብ ይበደላል፤ ይሰቃያል። የወያኔ የኤኮኖሚ እድገት የሚጠቅመው ለወያኔ ብቻ ነው። የወያኔ ውሸት ነው። የእድገት መለኪያው የተዛባ ነው። የታገልነውና የምንታገለው የሕዝብ ለሆነች ኢትዮጵያ ነውና ጥቂቶች ሲደላቸውና ሚሊዮኑ ሕዝብ ሲሰቃይ ሀገር አለፈላት ማለትን ልንቀበለው ቀርቶ ልንሰማውም አንፈልግም። ባዕዳን የራሳቸው ጥቅም አላቸውና ቡችሎቻቸውን ቢያዳንቁ ልንደናገር አይገባም። ግፋ ቢል ቀዳዳቸውን ጨምዳዳ ነው የሚሉት። ከሕዝባችን አንጻር ምንም ያለፈልን የለም፤ እድገት የለም፤ ድህነት ባሰ እንጂ አልቀነሰም፤ መከራው ከፋ እንጂ ዝቅ በረድ አላለም። ሁኔታውን ለመለወጥ ትግል መፋፋም አለበት፡፡ ሌላ መልዕክትን ተጨባጩ ሁኔታ እየሰጠን አይደለም።

ጸረ ወያኔው ትግል ይፋፋም!